# የአስቆሮቱ ይሁዳ

## የአስቆሮቱ ይሁዳ አሟሟት

በማቴዎስ 27:5 እና ሐዋርያት ስራ 1፡18 ?

- መጽሐፍ ቅዱስ ይጋጫልን ?

✓ መልስ ለጠያቂወቻችን !

**CHRISTIAN ANSWER CHANNEL**

Henock Abebe

# የአስቆሮቱ ይሁዳ

የአስቆርቱ ይሁዳ ከ12ቱ የክርስቶስ ደቀመዛሙት መካከል አንዱ የነበረ የኢየሱስ ተከታይ ነው ፡፡ ይሁዳ የኢየሱስ አገልግሎት የአይን ምስክር የነበረ ታእምራቱን ያየ ትምህርቱን የሰማ ደቀመዝሙር ነበር ፡፡

ይሁዳ በደቀመዛሙርቱ መካከል ገንዘብ ያዥ ነበር የሚሰጠውን መባ የሚያስቀምጡት እርሱጋ ነበር  ይሁዳም እርሱጋ ከሚቀመጠው ገንዘብ ላይ ለራሱ **ይሰርቅ** ነበር ፡፡

- ስለ ስምዖንም ልጅ ስለ አስቆሮቱ ይሁዳ ተናገረ፤ **ከአሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነ** እርሱ አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ አለውና።

(የዮሐንስ ወንጌል 6:71)

- 4፤ ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ።

5፤ ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሽጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው? አለ።
6፤ ይህንም የተናገረ <u>ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ</u> ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው።

ዮሐንስ ወንጌል 12፥4-6)

## ይሁዳ ገንዘብ ይወዳል በዚህም ምክንያት

- እርሱጋ ከሚቀመጠው ገንዘብ ይሰርቅ ነበር
- ለክርስቶስ የቀረበው ወድ ሽቶ ኢየሱስ ከሚቀባው ይልቅ ተሸጦ ወደ ገንዘብ ቢቀየር ይፈልጋል
- በመጨረሻም ኢየሱስን በ30 ዲናር ሸጠው

ዮሐ 12:6, ማቴ 26:15-16

# የአስቆሮቱ ይሁዳ አሟሟት

የአስቆሮቱ ይሁዳ ጌታን በ30 ዲናር ከሸጠ ቦሀላ ሰላም አላገኘም ኢየሱስ ላይ እንደፈረዱበት ካየ ቦሀላ ወደ ካህናቱ አለቆች ሄዶ ንጹህ ደም አሳልፎ እንደሰጠ ቢነግራቸውም እነሱ አልተቀበሉትም በጸጸት ሰላሳ ዲናሩን በቤተ መቅደስ በትኖ ወጣ ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ታሪክ ሁለት የአዲስ ኪዳን ጸሐፊወች ወንጌላዊ ማቴወስ በማቴወስ ወንጌል 27:5 እና ወንጌላዊ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 1:18 የዘገቡት ሲሆን ከእነኚህ ሁለት ጥቅሶች በመነሳት ሙስሊም ወንድሞቻችንና አንዳንድ መጽሐፍ የማይቀበሉ ሰወች መጽሐፍ **ቅዱስ ይጋጫል** ለማለት ይሞክራሉ ምክንያታቸው ደግሞ

ማቴወስ ይሁዳ **ታንቆ ሞተ** ሲል ሉቃስ በሐዋርያት ስራ ላይ **ሆዱ ተዘርግፎ ሞተ** ይለናል በማለት ሁለቱ ዘገባወች ይጋጫሉ ይላሉ ፡፡

## በእርግጥ ሁለቱ ክፍሎች የሚተጋገዙ ወይስ የሚጋጩ ?

የማቴወስ ወንጌል ጸሐፊ ወንጌላዊ ማቴዎስ በምዕራፍ 27:5 ላይ እንዲህ ይላል

- ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ። (የማቴዎስ ወንጌል 27:5)

በሌላ በኩል የሐዋርያት ሥራ ፀሐፊ ወንጌላዊ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 1:18 ላይ ስለ ይሁዳ እንዲህ ይለናል

- ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ፤"

(የሐዋርያት ሥራ 1:18

እነኚህን ሁለት ክፍሎች ይጋጫሉ ብሎሙግት ማቅረብ መጽሐፍንና የጸሐፊወቹን የአጻጻፍ ስልት ካለማወቅ የመነጨ ነው ፡፡ ሉቃስም ሆነ ማቴዎስ የራሳቸው የአጻጻፍ ስልት ያላቸው ለተለያዩ ተደራሲያን የጻፉት ሲሆን ሁለቱም የአስቆሮቱ ይሁዳን መሞት ላይ ይስማማሉ ፡፡

ማቴዎስ ይሁዳ ታንቆ እንደሞተ ሲነግረን ሉቃስ ደግሞ በግንባሩ ተደፍቶ አንጀቱ እንደተዘረገፈ ይነግረናል ፡፡

ሁለቱም ክፍሎች እርስ በእርስ የሚቃረኑ ሳይሆኑ የሚተጋገዙና ተጨማሪ ማብራሪያ የሚሰጡ አንድ አይነት ውጤት ያላቸው የተለያዩ የአገላለጽ መንገዶች ናቸው ፡፡

ማቴወስ በዝርዝር ስለ ይሁዳ አሟሟት አልገለጸም ቀጥታ ይሁዳ ታንቆ እንደሞተ ይነግረናል ፡፡

ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ ደግሞ ይሁዳ እንዴት እንደሞተ ከታነቀ ቦኃላ ያለውን ሁኔታ ይነግረናል ፡፡

እነኚህን ሁለት ክፍሎች ውስጥ መጋጨት ወይም መቃረን ሳይሆን መደጋገፍ ወይም አንዱ አንዱን በደንብ ያብራራዋል ይህ ማለት ማቴወስ በ27:5 ላይ የተናገረውን ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 1:18 ላይ በደንብ ያብራራዋል ፡፡

## ማቴዎስ ይሁዳ ታንቆ ሞተ ይለናል

ይሁዳ ኢየሱስ ላይ እንደተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ ብሩንም በቤተመቅደስ ጥሎ ታንቆ መሞትን ስለመረጠ ታነቀ

አንድ ሰው ሲታነቅ ገመድ ይዞ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ወይም ዛፍ ላይ በመውጣት ገመዱን በዛፉ ላይ አስሮ አንገቱን በገመዱ ውስጥ በማስገባት ይንጠለጠላል አንገቱ በመታነቁ አየር እያጣ ሲሄድ ትንሽ ከተፈራገጠ ቦኋላ ነብሱ ከስጋው ተለይታ ይሞታል ፡፡

ከሰአታት ቦኃላ ሰውነቱ ማበጥ ይጀምራል ከተሰቀለበት ከፍታ ቦታ ላይ ቁልቁል ይወድቃል የሞተው የይሁዳ አስክሬን ከመሬት ሲደርስ ከመሬት የሚጠብቁት አለቶች ግንባሩን የመፈንከት አቅም አላቸው ያበጠው ሰውነቱም በተለይ ሆዱ በወደቀ ሰአት ይፈነዳል በእዛን ሰአት አንጀቱ ይዘረገፋል ፡፡

ሉቃስ ስለ ይሁዳ አሟሟት በሐዋርያ ሥራ ላይ እንዷ ባለ ዝርዝር ዘገባ ነው ከታነቀ ቦኃላ ያለውን ያለውን ክፍል ሉቃስ ነው በደንብ የሚነግረን ፡፡

በከፍታ ቦታ ላይ ታንቆ ያልተንጠለጠለ ሰው እየተራመደ ወይቆ ግንባሩ ይከፈላል ሆዱ ይዘረገፋል ማለት አሳማኝ ባለመሆኑ ይሁዳ በከፍታ ቦታ ላይ ታንቆ የተንጠለጠለ እንደነበረ በመጨረሻም ከታነቀበት ገመዱ ተበጥሶ ወደ ምድር እንደወደቀና ሲወድቅም ግንባሩ

እንደተደፋ ከመካከሉም እንደተሰነጠቀ አንጀቱም እንደተዘረገፈ መረዳት ቀላል ነው ፡፡

ስለዚህ ማቴዎስ 27:5 እና ሐዋርያት ሥራ 1:18 የሚጋጩ ክፍሎች ሳይሆኑ የአንድ ክስተት የተለያዩ ተደጋጋፊና ይበልጥ አንዱ አንዱን የሚያብራራበት የተሳሰሩ የአንድ ታሪክ ሂደቶች ናቸው ፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ክፍሎች በተለያዩ ጸሐፊወች የተጻፉ ታሪኮች ትምርቶች ተደጋጋፊወች እንጂ የሚጋጩ አይደሉም ፡፡

## አንዲት ምሳሌ እናንሳና እንመልከት

በለጠ የተባለ አንድ ወጣት ሞቶ በመገኘቱ ምክንያት መርማሪ ፓሊሶች ስለ በለጠ አሟሟት ለማጣራት ሶስት ሰወች ለምስክርነት ጠርተው ቃላቸውን ሲሰሙ

ምስክር 1 ፡- አቤል - በለጠ ከስድስተኛ ፍቅ ላይ ራሱን ቁልቁል ወርውሮ ሞተ

ምስክር 2 ፡- ከበደ - በለጠ መሬት ወድቆ ጭንቅላቱ ከድንጋይ ተጋጭቶ ደሙ ፈሶ ሞተ

ምስክር 3፡- ሲሳይ - በለጠ መሬት ላይ ካለ ትልቅ ድንጋይ ላይ ተዘርግቶ ሰውነቱ በደም ተጠምቆ ነበር ፡፡

እነኚህ ሶስቱም ምስክሮች ስለ በለጠ መሞት ተናግረዋል አንዱ የተናገረው ከአንዱ **አይጋጭም** ይልቅ አንዱ የአንዱን ምስክርነት እያጠናከረ በለጠ እንዴት እንደሞተ ሙሉ ሐሳብ ይሰጠናል እንጂ ይህ ማለት ከሶስቱም ምስክሮች የተሰማው ቃል ሙሉ ሐሳቡ

በለጠ ከ6ተኛ ፎቅ ላይ ራሱን ወርውሮ ከመሬት ሲደርስ ድንጋይ ላይ እንዳረፈ ድንጋዩም ሰውነቱን እንደመታውና ሰውነቱም እንደደማ ከዛም በዚህ ምክንያት እንደሞተ ይነግረናል እንደዚህ አይነት ሙሉ ወጥ የሆነ ታሪክ ለመስማት የ3ቱም የምስክሮቹ ቃል ወሳኝ ነው ከአንደኛው ድርጊት ቀጥሎ ምን እንደተከሰተ ከአቤል ይልቅ ከበደ የበለጠ ይነግረናል

የሲሳይ ሲጨመርበት ሙሉ አሟሟቱን እናገኘዋለን ይሄ የአንዱ ምስክርነት ከአንዱ እንደሚጋጭ ሳይሆን የአንዱ ምስክርነት ከሌላው ጋር ተጨምሮ ሙሉ ታሪክ የሚሰጠን የተብራራ ሐሳብ እንደምናገኝ የሚያሳይ ነው ::

**የይሁዳም አሟሟት** በማቴወስና በሉቃስ ሲዘገብ እንዲህ ነው ለማቴወስ ዘገባ ማጠናከሪያ ሉቃስ ስለነገሩ ተጨማሪ **አዳዲስ** ማቴወስ ያልጠቀሳቸውን በመጥቀስ ስለ ይሁዳ አሟሟት ይበልጥ ያብራራልናል ስለዚህ ሉቃስ ስለ ይሁዳ አሟሟት ተጨማሪ ሐሳብ ማቴወስ ባለው ላይ ይጨምርልናል የሁለቱን ሐሳብ በማጣመር ሰፋ ያለ እውነታን እንረዳለን ::

# ማጠቃለያ

ይሁዳ ራሱን ሰቅሎ ታንቆ ሞተ (ማቴ 27:5) የታነቀበት ገመድ ተበጥሶ የይሁዳ አስክሬን ወደ ምድር ወደቀ በመታነቁ ምክንያት ያበጠው ሰውነቱ ከምድር ሲደርስ ፈነዳ አንጀቱም ተዘረገፈ ጭንቅላቱም በአለት ላይ በማረፉ ተሰነጠቀ ፡፡

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው የተጻፈውም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው ፡፡ በማቴዎስና በሐዋርያት ሥራ 1:18 መካከል ምንም ግጭት ወይም መቃረን የለም ሁለቱም ክፍሎች የአንድ ክስተት (የይሁዳ ሞት) የተለያዩ ዘገባወች ናቸው መጣረስ ሳይሆን መደጋገፍ አንዱ አንዱን ይበልጥ የሚያብራሩ ተጨማሪ ሐሳብን የሚጨምሩ ክፍሎች ናቸው ፡፡

## CHRISTIAN ANSWER CHANNEL

በቻናሎቻችን ለተለያዩ ጥያቄወች ምላሽና እንዲሁም አጫጭር መንፈሳዊ ጽሁፎችን እናቀርባለን ፡፡

ቻናሎቻችንን ተቀላቀሉ ለሌሎችም አጋሩ

- @Christian_Answer
- @chridtianAnswer

እንዲሁም ለአስተያየት፣ ለምክር ለተግሳጽ ለጥያቄም ጭምር በ

- @JapethAb ያግኙን

አዘጋጅ @Christian_Answer channel